የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ

Commercial Bank of Ethiopia

# ጋዜጣዊ መግለጫ

## የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የ2009 ዓ.ም ዓመታዊ ዕቅድ አፈጻጸም አጭር መግለጫ

### 1. መግቢያ

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በአለፉት 74 ዓመታት የአገልግሎት ዘመኑ ከሀገሪቱ ሁለንተናዊ የልማት እንቅስቃሴ ጋር የቅርብ ቁርኝት ያለው ባንክ ነው፡፡ የሃገሪቱን የልማት ፕሮጀክቶች እና አጠቃላይ የቢዝነስ እንቅስቃሴ በፋይናንስ በመደገፍ፣ የባንክ አገልግሎት በመላ ሃገሪቱ በማስፋፋትና አዳዲስና በቴክኖሎጂ የተደገፉ የባንክ አገልግሎቶችን በማስተዋወቅ ረገድ ግንባር ቀደም ሚና እየተጫወተ የሚገኝ ባንክ ነው፡፡

ባንኩ በአሁኑ ወቅት እ.ኤ.አ ከ2015/16 እስከ 2019/20 የሚዘልቀውን ሁለተኛ ስትራቴጂያዊ ዕቅድ በመተግበር ላይ ይገኛል፡፡ ያለፉት ሁለት ዓመታት አፈጻጸሞች እንደሚያመለክቱት ባንኩ ባስቀመጠው ስትራቴጂ መሰረት እየተጓዘ ይገኛል፡፡ አፈጻጸሞቹም ባንኩ እ.ኤ.አ በ2025 ዓለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ የንግድ ባንክ ለመሆን ያስቀመጠውን ራዕይ ለማሳካት በሚችልበት ትክክለኛው መንገድ ላይ መሆኑን አመላክተዋል፡፡

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ማኔጅመንት የ2016/17 ወይም የ2009 የበጀት ዓመት የዕቅድ አፈጻጸም ግምገማ እ.ኤ.አ ከሐምሌ 17 እስከ 22 ድረስ በአዲስ አበባ ከተማ አካሂዷል፡፡ የባንኩ የ2016/17 (2009 ዓ.ም) ዕቅድ አፈጻጸም አጭር መግለጫም እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

### 2. የተቀማጭ ገንዘብ አሰባሰብ

በባንኩ ስትራቴጂ ላይ ከተቀመጡት ዐበይት ጉዳዮች አንዱ ተቀማጭ ገንዘብን በከፍተኛ ደረጃ በማሳደግ በመንግስትና በግሉ ዘርፍ ለተያዙ ፕሮጀክቶች እና ልዩ ልዩ የልማት እንቅስቃሴዎች ብድር ለማቅረብ የሚረዳ አቅምን ማሳደግ የሚረዱ ተግባራትን ማከናወን ነው፡፡ ይህን ዕውን

ለማድረግ የህብረተሰቡን የቁጠባ ባህል ለማሳደግ የሚረዱ ልዩ ልዩ ዕቅዶች ተተግብረዋል፡፡ ህብረተሰቡ ስለቁጠባ የተሻለ ግንዛቤ እንዲኖረው ከማድረግ አንስቶ በሽልማት ላይ የተመረኮዘ ቁጠባን በማበረታታት በርካታ ተግባራት ተከናውነዋል፡፡ በነዚህ ተግባራት አማካኝነትም በበጀት ዓመቱ 76.4 ቢሊዮን ብር ተጨማሪ ተቀማጭ ገንዘብ ማሰባሰብ የተቻለ ሲሆን፣ ይህ ክንውን የባንኩን ጠቅላላ ተቀማጭ ገንዘብ በ2008 ዓ.ም የበጀት ዓመት ከነበረበት ብር 288.4 ቢሊዮን ወደ ብር 364.9 ቢሊዮን ማድረስ ችሏል፡፡ ይህም ክንውን የባንኩን በሀገሪቱ የሚከናወኑ የተለያዩ የልማት ፕሮጀክቶችና የቢዝነስ እንቅስቃሴዎች በፋይናንስ የመደገፍ አቅም ያጎለበተ ነበር፡፡

## *3. የብድር አሰጣጥና አሰባሰብ ክንውን*

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ተቀማጭ ገንዘብን እና ከብድር ተመላሽ ገንዘብን በማሰባሰብ በብድር መልክ ተመልሶ ወደኢኮኖሚ እንዲገባ ያደርጋል፡፡ በበጀት ዓመቱ ብር 64.6 ቢሊዮን ከብድር ተመላሽ መሰብሰብ የተቻለ ሲሆን፣ ብር 94.5 ቢሊዮን አዲስ ብድር (disbursement) ለልዩ ልዩ የሥራ መስኮች ፣ ኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች እና ደንበኞች ማቅረብ ተችሏል፡፡

## 4. የውጭ ምንዛሪ ግኝት

የሀገሪቱን የልማት ጥያቄ በአግባቡ ለመመለስ እንዲቻል እንደተቀማጭ ገንዘብ ሁሉ የውጪ ምንዛሪ ግኝትን ለማሳደግ በርካታ ተግባራት ተከናውነዋል፡፡ በዓመቱ በተደረጉ እንቅስቃሴዎችም ከወጪ ንግድ፣ ከሃዋላ፣ ከውጭ ምንዛሪ ግዢና ሌሎች አገልግሎቶች 4.5 ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር ማግኘት ተችሏል፡፡

## 5. የገቢ እና ትርፍ አፈፃፀም

ባንኩ በበጀት ዓመቱ ካደረጋቸው አጠቃላይ እንቅስቃሴዎች ብር 31.9 ቢሊዮን ገቢ ያገኘ ሲሆን፣ ከታክስ በፊት የብር 14.6 ቢሊዮን ትርፍ ማግኘትም ተችሏል፡፡

## 6. ጠቅላላ ሀብት እና ካፒታል

የባንኩ ጠቅላላ ሀብት ብር 485.7 ቢሊዮን ደርሷል፡፡ መንግሥት የባንኩን ካፒታል በማሳደግ የማበደር አቅሙን እንዲሁም ጠቅላላ አቋሙን ለማሳደግ በወሰነው መሰረትም የባንኩ ካፒታል ወደ 40 ቢሊዮን ብር አሳድጓል፡፡ ይህም ክንውን የባንኩን የማበደርና የመሪነት ሚና አጠናክሮ ለማስቀጠል የሚያስችል አቅም ፈጥሯል፡፡

## 7. የአገልግሎት ተደራሽነትና የኤሌክትሮኒክ ባንኪንግ አፈጻጸም

ቅርንጫፍ ከፈታ፣ ልዩ ልዩ አዳዲስ የቁጠባ ሂሳቦችን ማስተዋወቅ እና የኤሌክትሮኒክ ባንክ አገልግሎቶች ባንኩ ተደራሽነቱን ለማስፋት ተግባራዊ የሚያደርጋቸው እንቅስቃሴዎች ናቸው፡፡ ከዚህ አንፃር በበጀት ዓመቱ በርካታ ተግባራት ተከናውነዋል፡፡

በሃገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች 85 አዳዲስ ቅርንጫፎች በመክፈት የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ቅርንጫፎችን ብዛት 1,222 ማድረስ ተችሏል፡፡ የባንኩን ተደራሽነት ለማስፋት በተደረገው ጥረት 2.7 ሚሊዮን ተጨማሪ ደንበኞችን ማፍራት የተቻለ ሲሆን፣ ሂሳብ ያላቸው የባንኩ ጠቅላላ ደንበኞች ቁጥርም 15.9 ሚሊዮን ደርሷል፡፡

የኤሌክትሮኒክ የባንክ አገልግሎቶችን ተደራሽ ከማድረግ አንፃርም በአመቱ 1.6 ሚሊዮን አዲስ የባንክ ካርዶችን በማሰራጨት በደንበኞች እጅ የሚገኙ ቪዛ ካርዶችን ጠቅላላ ብዛት 3.7 ሚሊዮን ማድረስ ተችሏል፡፡

የሞባይልና የኢንተርኔት የባንክ አገልግሎትን በተመለከተም በበጀት ዓመቱ በርካታ ደንበኞችን ማፍራት ተችሏል፡፡ በዚህ መሰረት የሞባይል የባንክ አገልግሎት ተጠቃሚዎች ቁጥር 1.4 ሚሊዮን፣ የኢንተርኔት የባንክ አገልግሎት ተጠቃሚዎች ደግሞ ከ25 ሺህ በላይ ደርሷል፡፡

በበጀት ዓመቱ ለደንበኞች አመቺ በሆኑ ስፍራዎች ተጨማሪ 612 የኤ.ቲ.ኤም (ATM) እና 874 የፖስ (POS) ማሺኖችን በማኖር የባንኩን ኤ.ቲ.ኤም ቁጥር 1,501፣ የፖስ ማሽኖች ደግሞ 6,811 ማድረስ ተችሏል፡፡

የባንኩን ተደራሽነት ይበልጥ ለማስፋት የውክልና ባንክ አገልግሎት ለመጀመር እንቅስቃሴ ሲደረግ ቆይቷል፡፡ በበጀት አመቱም (CBE Birr) የውክልና ባንክ አገልግሎት እንዲጀመር ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ፈቃድ ተገኝቶ አገልግሎቱን በሙከራ ደረጃ መስጠት ተጀምሯል፡፡

## 8. የሰው ሀብት ግንባታ

ባንኩ ለደንበኞቹ የሚሰጠውን አገልግሎት ቀልጣፋ ከማድረግ አንፃር የሰው ኃብት ልማት በዋነኛ ስትራቴጂነት ተወስዷል፡፡ በአመቱ የ6,297 አዳዲስ ሠራተኞች ቅጥር በማከናወን የባንኩን የሰው ኃይል 33,706 ሺህ ማድረስ ተችሏል፡፡ የባንኩን ሠራተኞች አገልግሎት አሰጣጥ አቅም ለማዳበር ትልቅ ፋይዳ ያላቸው ሥልጠናዎችም ተሰጥተዋል፡፡

## 9. በውጪ ሀገሮች ቅርንጫፍ ከፈታ

በተለያዩ የአለማችን ክፍሎች የኢትዮጵያ ንግድ ባንክን ቅርንጫፎች ለመክፈት የሚያስችሉ ጥናቶች እየተደረጉ ሲሆን፣ በተለያየ ደረጃ ላይም ይገኛሉ፡፡ በተጠናቀቀው የበጀት አመት የባንኩ የጂቡቲ ቅርንጫፍ ተከፍቶ አገልግሎት መስጠት ጀምሯል፡፡

## 10. የህንፃ ግንባታ ፕሮጀክቶች አፈፃጸም

የባንኩን የአገልግሎት አሰጣጥ ቀልጣፋ ለማድረግ ከሚረዱ ተግባራት መካከል አመቺ የቢሮና የአገልግሎት መስጫ ስፍራዎች ዋንኛና አስፈላጊ ግብአት እንደሆኑ ይታመናል፡፡ ከዚህ በመነሳት ባንኩ በርካታ የግንባታ ፕሮጀክቶችን በክልል ከተሞችና በአዲስ አበባ ከተማ እያካሄደ ይገኛል፡፡

እጅግ ዘመናዊ የሆነው የባንኩ የዋና መ/ቤት ህንፃ ግንባታ በተቀመጠለት የጊዜ ሰሌዳ መሰረት እየሄደ ሲሆን፣ በአሁኑ ጊዜም 43 ከመቶ የሚሆነው የዲዛይንና የግንባታ ስራ ተከናውኗል፡፡ በአዲስ አበባ ከተማ እየተገነቡ ካሉ ፕሮጀክቶች መካከልም በልደታ አካባቢ የተገነባውና “ዛጉዌ” የሚል ስያሜ የተሰጠው ሁለገብ ህንፃ፣ እንዲሁም በመርካቶ አካባቢ “ገዳ” የሚል ስያሜ የተሰጠው ህንፃ ግንባታ ተጠናቀው ወደ አገልግሎት እየተሸጋገሩ ይገኛሉ፡፡

## 11. ማጠቃለያ

የ2016/17 (2009 በጀት ዓመት) የዕቅድ አፈጻጸም በጣም አርኪ ነበር ማለት ይቻላል፡፡ በተለይ በተቀማጭ ገንዘብ አሰባሰብ በኩል በባንኩ ታሪክ እጅግ ከፍተኛ የሚባል አፈጻጸም ማስመዝገብ ተችሏል፡፡ የባንኩን የ2025 ራዕይ ከማሳካት አንፃር ትልቅ ቦታ የተሰጣቸው የሰው ኃብት ልማት ስትራቴጂ፣ በባንኩ የፕሮጀክት ጽ/ቤት የተያዙ የአይቲ ፕሮጀክቶች እና ተያያዥ ፕሮጀክቶች በአብዛኛው እየተጠናቀቁ ወደ ትግበራ እየተሸጋገሩ ይገኛሉ፡፡

በባንካችን የገንዘብ ድጋፍ በርካታ የቁጠባ ቤት ልማት ፕሮጀክቶች እየተከናወኑ እንደሆነ ይታወቃል፡፡ በተጠናቀቀው አመትም 972 የ40/60 ቤቶች ተጠናቀው ግልጽነትን በተላበሰ የዕጣ አወጣጥ ሥነ-ሥርዓት ለተጠቃሚዎች ተላልፈዋል፡፡

በባለፉት ዓመታት እንደኢትዮጵያ ላሉ የግብርናና ተያያዥ ምርት አቅራቢዎች የአለም ገበያ ብዙም የተመቸ አልነበረም፡፡ በምርቶች ዋጋ መዋዠቅ የተነሳ በጠቅላላ በሀገሪቱ የውጪ ምንዛሪ ግኝት ላይ በተወሰነ ደረጃ አሉታዊ ተጽእኖ አሳርፏል፡፡ ይህ ሁኔታ በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የውጪ ምንዛሪ ግኝት ላይም የራሱን ተጽእኖ ማሳረፉ አልቀረም፡፡ ይሁንና የባንኩ አፈጻጸም አበረታች ነበር ማለት ይቻላል፡፡